ዕለት ነው። አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባው እኛ ኢትዮጵያውያን በአንድ አምላክ በማመን ከእስራኤልያውያን የማያንስ የጊዜ ታሪክ እንዳለንና ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመቀበል ደግሞ የመጀመርያዎች ከሚባሉት ታላላቅ ህዝቦች ውስጥ አንድኛው መሆናችንን ነው። የታሪክ መጽሀፍቶች እንደሚያስረዱት የክርስትናን ህይማኖትን በማስፋፋት

*ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና የተስፋፋው ከአውሮፓ በመጡ ሚስዮኖች ሳይሆን ከክርስቶስ ማስተማር አንስቶ በደቀመዝሙሮችና በአባቶቻችን መንፈሳውያን ነው።*

ደግሞ

ኢትዮጵያኖችመንፈስያውያን እንዲሁ ከመጀመርያዎቹ አንደኛው መሆናቸውን ነው።

አባቶቻችን ቄሶች፤ ደብተራዎች፤ ባህታውያን፤ መነኮሳቶች፣ ዲያቆኖች እንዲሁም መሣፍንቱና ነገስታቶች የክርስትና እምነትን በመላው አገሪቱ በሚያዳርሱበት ጊዜ አውሮፓውያኖች ሮማውያንን ጨምሮ የሚያመልኩት በጣኦት ነበር።



በመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት፤
ባህልና ታሪክ ኮሚቴ የሚዘጋጅ

የጥንት ነገስታቶች አስተዳድራቸውን ከመንፈሳዊ እውቀታችው ጋር አዋህደው ራሳቸውም በመመንኮስና መጽህፍቶችን በመጻፍ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይና እንዲስፋፋ ታላቅ አስተዋጾ አድርገዋል። ይህንን ለረጅም ጊዜ ያቆዩልንን መንፈሳዊ ውርስ በቀናዒነት መጠበቅ ደግሞ የዚህ ትውልድ ህላፊነት ነው። ቸር ይግጠመን።




መከነ ስላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን
አድራሻ፡ 8990 Grove street, Elk Grove, CA 95624
Tel (916) 690 8794/ (916) 743 4136/ (916) 868-8032
www.sacramentoselassie.com



# መልዕክተ መካነ ሥላሴ



## ታቦት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እንዲሁም በኢምነቱ ተከታዮች ታቦት ትልቅ ቦታ ያለው የእምነት ማእከል ነው። በአለም ላይ ከሚገኙ በመቶዎች ከሚቆጠሩ የክርስትና እምነት ተከታዮች ታቦትን የእምነት ማእከል አድርጋ ያቆየችው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንና የእምነቱ ተከታዮች የሆኑት ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። ታቦት የኢትዮጵያውያን ብቸኛ ቅርስ ከመሆንም ባሻገር ኢትዮጵያ ለክርስትና እምነት መቀበልና መስፋፋት የመጀመርያ ከሆኑት ጥንታዊ አገሮች መካከል አንዷ መሆኗን የሚያመለክት ቋሚ ማስረጃ ነው።

በተጨማሪም ታቦት ኢትዮጵያዊነታችንና ነፃነታችን ለማስከበር ልዩ ህይል የሚሰጥ ምልክት ሆኖ ለብዙ ሺህ አመታት አገልግሏል። በተለያዩ ጊዜያት በመንግስትነት ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት ነገስታቶች አገሪቷን በጠላትነት ለመውረር የተነሱትን የውጭ ወራሪዎች የመከቱበትና አገሪቷን በአንድነት ያቆዩበት መንፈሳዊ ብርታት ያገኙትታቦትን ማዕከል ባደረገ ኦርተዶክስ እምነት ፀንተው መሆኑን ገድላቸውና ታሪካቸው ይናገራል።

ሳክራሜንቶ መካነ ስላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤትክርስትያን በራሪ የትምሕርት ማስራጫ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምነት መሰረት ማንኛውም ቤተክርስትያን ያለታቦት ተተክሎ ለእምነቱ ተከታዮች የቅዳሴም ሆነ ሌሎች በእምነታችን አስፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ ግልጋሎቶች መስጠት አይችልም።

በሐዲስ ኪዳን የታቦትን ሐያልነት ተነግሯል የዮሐንስ ራእይ 11፥19 በሰማይም ያለው የእግዚአብሄር መቅደስ ተከፈተ፤ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፤ መብረቅና ድምፅም ነጎድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ። በዚች መለክተ መካነ ሥላሴ እትም የታቦት ምንነትና ለምን የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ የእምነት ማእከል መሆኑን በአጭሩ እንተነትናለን።

የታቦት ታላቅነት በኢትዮጵያ ውስጥ መቀበል የተጀመረው በቀዳማዊ ምኒሊክ (የንግስት ሳባ ልጅ) ጊዜ ጀምሮ መሆኑን አያሌ ኢትዮጵያውያን፡ ዓረብና የአውሮፓ ፀሃፊዋች ዘግበዋል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ደግሞ ታቦት እግዚአብሄር ከልጆቹ ጋር የመሆኑ ምልክት ነው እንጂ በእግዚአብሔር ምትክ የሚመለክ ጣኦት አለመሆኑን እምነታችን ያስተምራል።

*አንሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣርያችን ለመድሃኒታችን እግዚአብሔ ር ምስጋና ይግባው።*



ከክርስቶስ ልደት ሶስት ሺህ አመት በፊት የገናናዋ ንግስት ሣባ ልጅ ምንሊክ ወደ እየሩሳሌም አባቱን ንጉስ ሰለሞንን ለመጎብኘት ሄደ። በእየሩሳሌምም መምጣቱ በተሰማበት ጊዜ አባቱ ንጉስ ሰለሞን ደስታ ተሰማው፤ ታላቅም አቀባበል አደረገለት።

ቀዳማዊ ምኒሊክም እየሩሳሌም ቆይታው ወቅት ለሶስት ዓመት የኦሪትን ሕግ ሲያጠነ ቆየ። ወደ አገሩ ኢትዮጵያ በሚመለስባትም ወቅት አባቱ ንጉሥ ሰለሞን ለቀዳማዊ ምኒሊክ ወደ12000 የሚጠጉ እስራኤላውያን አጃቢ ሰጥቶ ሸኘው። ከነዚህም ውስጥ በመንፈሳዊ እውቀታቸው የላቁ እንደነ አዛርያስ የመሳሰሉ ነበሩበት። ንጉስ ሰለሞን ከሰጠው ትልቁ ስጦታ አንዱ የታቦት ጽዮን ምስል፣ የወርቅ መጎናፀፍያ፣ መጽሃፍትና ነዋየ ቅድሳት ይገኙበታል።

አዛርያስ በቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ሕልም ታየው። በተነገረው ሕልም መሰረት በምስጢር ሔዶ እውነተኛይቱን እግዚአብሔር ለሙሴ በእጁ የሰጠውን ታቦት በሽሉክታ ከቤተመቅደሱ አውጥተው ጉዟቸውን ወደ ኢትዮጵያ አቀኑ። ይህም በተሰማበት ወቅት ንጉስ ሰለሞን ታቦትን ለማስማለስ እስከ ጋዛ ብሎም እስከ ግብጽ ድረስ አሳደዳቸው። ሆኖም ግን ደርሶባቸው ታቦቱን ለማስመለስ አልተሳካለትም። ቀዳማዊ ምንሊክም ታቦተ ጽዮንን ይዞ ኢትዮጵያ ገባ። ከዚህ



የይሁዲ ህይማኖት በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፋ። የኢትዮጵያ መንፈሳውያንም ወደ እየሩሳሌም የሚያደርጉት ጉዞ ተስፋፋ ከእስራኤል ጋር ያለን ግኑኝነት ተጠናከረ። የሙሴ ጽላት ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጣበት ጊዜ አንስቶ በተለያየ የችግር ወቅት ጽላቷን ሊያጠፏት የሚሞክሩትን ጠላቶች ለመቋቋም በተለያዩ ገዳማት በምስጢር ተቀምጣለች። ሆኖም ዋናው የታቦቱ መቀመጫ አክሱም የምትገኘው ጽዮን ማርያም መሆኑ ይታመናል። ስልዚህ በየበለጥ ለመረዳት ክብረ ነገስትንና ሌሎች የውጪ ፀሐፊዎች የጻፉትን መጽሃፍቶችን ያንብቡ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን አጣምሮ 81 መጽሃፎች በሚይዘው መፅህፍ ቅዱስ ተዘክሮ በሚገኘው የፈጣርያችን የመድሃኒታችን የእግዚአብሄር ቃል ሳይጨምር ሳይቀነስ ምንም መሻሻል ሳያደርግበት ሙሉ ቃሉን ይቀበላል።

የሐዋርያት ሥራ 8፥ 26-39 ላይ እንደሚያስተምረው ኢትዮጵያውያን ከክርስቶስ ሥራ ጋር የተዋወቁትና ስለክርስትና እምነት ያወቁት ራሱ ክርስቶስ በሕይወት በነበረበት ጊዜና ደቀመዛሙርቶችም ለመጀመርያ ጊዜ አሕዛብን ማስተማርያ የሚረዳ የመንፈስ ቅዱስ ሃይል ባረፈባቸው ወቅት በጰራቂሊጦስ

ሐዋ ሥራ 8፡26 ፊሊጶስም አኡን ከፈተ ከዚሕም መፅህፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት።…ፊሊጵስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደውኀው ወረዱ፥